# ይድረስ ለፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

ከመዓዶት ይሁን

ማክሰኞ መስከረም ፲፫ ቀን ፪ሺህ፫ ዓ. ም. "የትጥቅ ትግልና ግራ የሚያጋባ አስተያየት" በሚል የጻፉትን መጣጥፍ አንብቤ በእውነት እኒህ አንቱ ተብለው የነበሩ ሰው የጻፉት ነውን? የሚል ጥያቄ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። በሌላ በኩል ግን ከጥቂት ወራት  የጻፉትን ላነበበ፣ በዚህ ጽሁፍዎ አይገረምም። ባለፈው ጽሁፍዎ "አንድም ሰው (ወዳጆቼ ሁሉ) አልተረዳኝም፤ ሁሉም ተቸተውኛል" ያሉትን ላስታውስዎ። አንድ ሰው በሩቅም በቅርብ ያለው ተሳስተዋል ብሎ ሁሉም ሲተችዎት ቆም ብለው ያስባሉ የሚል ተስፋ ነበረኝ። አለመታደል ሆኖ "ያዳቆነ ሰይጣን... " እንዲሉ ካለፈው ብሶብዎት የግንቦት 7 ቀንደኛ ደጋፊ ሆነው ለምን ይህን  ፀረ-አማራ፣ አገር አጥፊና ፀረ-አንድነት የሆነውን ድርጅት በየትኛው የማሳመኛ ምክንያት መነሻነት ሊደግፉት እንደተነሱ አልገባኝም። ይህን ከእርስዎና ከአንድዬ በስተቀር የሚያውቀው የለም።

ግንቦት 7 በኤርትራ በኩል ይደረጋል እያለ የሌለው ጦርነት የምንቃወምበት ምክንያቱ ብዙ ነው።  ቢያንስ ላለፉት 17 ዓመታት ተቃዋሚ ነን ያሉ ብዙ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ኤርትራ ገብተው ያሰቡትን ትግል ማድረግ እንደማይችሉ የዓይን እማኞችና የአካል ምስክሮች ያረጋገጡት መሆኑ፤ እንታገላለን ብለው የሄዱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በተለይም የአማራው ልጆች ኤርትራ ከገቡ በኋላ መገደላቸው፣ በዋሻና በኮንቴነር መታሰራቸውና ሕይወታቸው በተዓምር የተረፈው ደግሞ የሻዕቢያ ባሪያ ሆነው ማሽላ አጫጅ፣ መንገድና ድልድይ ሰሪ ሆነው በባርነት እንዲኖሩና ኤርትራን ለቀው እንዳይወጡ ድንበር ተዘግቶባቸው በግዳጅ እንዲኖሩ መደረጉ፣ የሻዕቢያ ባለስልጣኖች በግልጽ ወያኔ እንዲወድቅ እንደማይፈልጉ መናገራቸው፤ ከብዙ በጥቂቶቹ ናቸው። ይህንንም አሳምረው ያውቁታል። ዛሬ በግራ ጎንዎ ተነስተው የብርሃኑ ነጋ አጫፋሪ የሆኑበት ጉዳይ አልገባን አለ አንጂ።

ፕሮፌሰር፣ እርስዎ አብዛኛውን ሕይዎትዎን አንቱ ተብለው ታፍረው ተከብረው ኖረዋል። ዛሬ ባለቀ እድሜዎ አንድ እግርዎ ጉድጓድ በገባበት ሰዓት እንዲህ ዓይነት ቅሌት ውስጥ ለምንድን ነው የገቡት? ከእርስዎ ቀድመው ያለፉት ጓደኞችዎና ዘመዶችዎ የእርስዎን የወረደ ስራና ቅሌት ሳያዩ በማለፋቸው ብፁዓን ናቸው። በዚሁ ከቀጠሉ በእርስዎ መቃብር ላይ ከቤተሰቦችዎ በስተቀር ሌላ ኢትዮጵያዊ ተገኝቶ ነፍስዎን ይማር የሚልዎት አይመስለኝም። ምናልባት አትንኳቸው ያሉላቸው ግንቦቴዎች መጥተው ያደምቁት ይሆናል። ሳያውቁት ታመዋልና ምህረቱን ይላክልዎት።

ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይጠብቅ!